# የአቶ ኪሩቤል ዘውገ አጭር የሕይዎት ታሪክ፤

አቶ ኪሩቤል ዘውገ ከአባቱ ከቀኝአዝማች ዘውገ ገብረኪዳን እና ከእናቱ ከወ/ሮ ማሚቴ ስመንጉሥ በ1949 ዓ/ም (እ.አ.አ. 1957) በአዲስ አበባ ተወለደ።

አንደኛ ደረጃን በአስፋወሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በተፈሪ መኮንን ት/ቤት በከፍተኛ ማዕረግ አጠናቋል።

አቶ ኪሩቤል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ፣ አገሩን በወታደራዊ ሙያ ለማገልገል በነበረው ጽኑ ፍላጎት ስመ-ጥር የነበረውን የኢትዮጵያ ምድር ጦር አየር ወለድ ክፍል በመቀላቀል ለአንድ አየር ወለድ አባል በራሪ ነብር ለመባል ብቁ የሚያደርገውን አጠቃላይ ወታደራዊ ሥልጠና አጠናቅቆ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በሙያው አገልግሏል።



ወቅቱ የአብዮት ነውጥ የሰፈነበት ጊዜ ስለነበር በአገራችን በኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥ ለማምጣትና ደርግ የዜጎችን መብት በሚያከብር የሲቪል አስተዳደር እንዲተካ አባል የሆነበት የአየር ወለድ ጦር ባደረገው እንቅስቃሴ አቶ ኪሩቤል ንቁ ተሣትፎ ካደረጉትት መኻል አንዱ ነበር።

ኪሩቤል በሠራዊቱ ውስጥ የተሞከረው የለውጥ እንቅስቃሴ በታሰበው መልክ ሣይሳካ ሲቀር ተስፋ ቆርጦ አልተቀመጠም፣ እንዲቀየር የታገለውን ወታደራዊ ደርግ ማገልገልም አልፈለገም ወይም በቀጥታ አገሩን ጥሎ አልተሰደደም። ቆራጡ ኪሩቤል ምርጫውን ያደረገውና የወሰነው ለፍትኀ፣ ለእኩልነትና ለአንድነት የሚደረገው ትግል ግቡን እስኪመታ ለራሱ የገባውን ቃል-ኪዳን አክብሮ ትግሉን መቀጠል ነበር። በመሆኑም ከአየር ወለድ አዛዥ ጀምሮ ተመሳሳይ ዓላማና ውሳኔ ከነበራቸው የትግል ጓደኞቹ ጋር በመሠለፍ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊትን /ኢሕአሠን/ በመቀላቀል በትግራይና በጎንደር በረሃዎችና ገጠሮች በተደረገው የትጥቅ ትግል ተዋጊና አዋጊ በመሆን ሙያዊ ብቃቱንና መንፈሰ ጠንካራነቱን፣ አገር-ወዳድነቱንና ለሕዝብ የነበረውን ፍቅር በተግባር ያስመሰከረ ጀግና ነበር።

አቶ ኪሩቤል ዘውገ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከትግል ሜዳና ከሚወዳት አገሩ መውጣት ቢገደድም፣ ለአገሩና ለሕዝቡ የነበረው ፍቅርም ሆነ ገደብ የሌለው በጎ ምኞት እስከ ሕይዎቱ ፊጻሜ አልተለዩትም። ከሱዳን እስከ ኬንያ፣ ከኬንያ እስከ ተለያዩ የአውሮጳ አገሮች ያዞረው የስደት ሕይዎት፣ በመጨረሻ እ.አ.አ. በ1980 ዓ/ም አሜሪካ በመምጣት እስከ ሕይዎቱ ፊጻሜ ድረስ ኑሮውን እዚሁ አድርጎ ቆይቷል።

አቶ ኪሩቤል የተለያዩ ሙያዎችና ተሰጥዖዎች የነበሩት ሲሆን የጤና መታወክ እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርቶ ይተዳደር ነበር።

አቶ ኪሩቤል በደረሰብት ከፍተኛ የልብ ህመም ምክንያት በቨርጂኒያ ሆስፒታል ሲታከም ቆይቶ የካቲት ፳፬ ቀን ፪ ሺህ ፱

**ዓ/ም** (March 4, 2017) **ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።**

**አቶ ኪሩቤል ትሁትና ተጫዋች፣ ሰው አፍቃሪና አክባሪ፣ ለጋስና ተግባቢ አገር-ወዳድ ኢትዮጵያዊ ነበር።**

**አምላክ ነፍሱን በገነት ያኑርልን።**

**አሜን።**



